ከቀሲስ አስተርአየ ጽጌ   ካንሳስ ሙዙሪ
nigatuasteraye@yahoo.com



# "እኔን ወደ በሐሩ ጣሉኝ"

ስለ ነነዌ ጾም ስናስብ የሰውን ጭንቅና ሥቃይ ከማይ "*ማእበሉ ጸጥ እንዲልላችሁ እኔን ከመርከቡ አውታችሁ ወደ በሐሩ ጣሉኝ*" ያለውን ነቢዩ ዮናስን እናስታውሳለን:: የነነዌ ጾም ከነገረ መለኮቱ ከታሪካችንና ከባሕላችን ጋር የተሳሰረ ነው:: አጉልቶ የሚያሳየውም የፈጣሪን መሐሪነትና ሰባዊ ርኅራኄን ነው:: ዳሩ ግን ነቢዩ ዮናስ የተናገረው: በኋላም ክርስቶስ "*ይህ ሕዝብ ያሳዝነኛል*" ሲል በቃል አስተምሮ በተግባር የፈጸመው መሐሪነትና ርኅራሔ አሁን ባለንበት በዚህ ዘመን፥ እንደ እምቧይ ካብ እየተናደ ነው:: "*ክርስቲያን ከሆናችሁ ከክርስትና በፊት በባቢሎን ይኖሩ የነበሩት ሰዎች የጾሙትን ለምን እናንተ ትጾማላችሁ?*" እያሉ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ውጭ ያሉ ሰወችም ነቀፌታና ትችት ይሰነዝራሉ:: ይህ ትችት እምነታችንን ታሪካችንንና ባሕላችንን ሁሉ እንድንዳስስ የሚአስገድድ፥ ኢትዮጵያዊ ስሜታችንንም ጥይት እንደ ሚቆሰቁስ ባሩድ የሚአደርግ ነው::

"*ማእበሉ ጸጥ እንዲልላችሁ እኔን ከመርከቡ አውጥችሁ ወደ በሐሩ ጣሉኝ*" የሚለውን ሰብአዊ ርሕራኄ ስለሚያስታውሰን ስለ ነነዌ ጾም ስንነጋገር፥ ትንቢተዮናስ በመባል በአራት አጫጭር ምዕራፎች የተጠቃለለውን አጭር መጽሐፍ መሠረት በማድረግ ነው:: የተሸከመው ሰፊ ቁም ነገር ብሉዩንና ሐዲሱን ያገናኘ ነው:: መጽሐፉን በማንበብ ብቻ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሙያዊ (ቴክኒካል) ያተረጓጎም ዘይቤን መረዳት አይቻልም:: ይህ መጽሐፍ እንደ ጋዜጣ ወይም የታሪክ መጽሐፍ የሚነበብ አይደለም:: ቅዱሳት መጻሕፍትን የምንቀርብበትን ዘይቤ ሌሎች መጻሕፍትን ከምንቀርብበት ለመለየት መድገም ብለው አባቶች እንዳስተማሩን: ሳንሰለች በሕይወታችን እየደጋገምን እንደምንመገበው እንጀራችን፥ እየደጋገምን የምናነበው: እያነበብን የምንደግመው የመንፈስ መግባችን ነው:: በመረሳት ላይ ባለው በግእዙ ቋንቋችን አንድም እያሉ ሊቃውንት አበው የነገሩንን፥ ከውጭ የተቀላወጠ ነገር ሳንጨምር፥ ፈጠራ ሳንደርትበት በትክክል ማስቀመጥ አለብን:: የሚነሱትን ሁሉ ጥያቄዎች በጥንት አባቶች መንገድ ከተመለከትናቸው መልስ ማግኘት ብቻ ሳይሆን፥ የዘመናችንን መሪወች ክፋትና ጭካኔ አጥርተው ያሳዩናል:: የራሳችንንም ድካም የምናይባቸው የሕሊና መስታወታወቶች ይሆኑናል::

ለሚነቅፉን ወገኖች በፍቅርና በትህትና ይህንኑ ሳንቀንስና ሳንጨምር ብንነግራቸው የእምነት ሰወች ከሆኑ ሌላ ተልእኮ ከሌላቸው፥ ልባቸውን በመመለስ እንደኛ ይጾሙት ይሆናል:: ያም ባይሆን ነቀፌታቸውን የሚያቆሙ ይመስለኛል:: ይልቁንስ ሁላችንም ተነቃፊወችም ነቃፊወቻችንም በኅብረት ልነረዳው የሚገባን ነገር እንዳለ ማሳሰብ እወዳለሁ:: በኦሮቶዶክስ ተዋህዶ እምነትና ሥርአት በጾምና በጸሎት በሱባኤና ትህርምት ላይ መሆን ችግር ሲመጣ ወይም የግል ነገር ሲገጥመን ብቻ አይደለም:: በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ሰወች ሲያደርጉት የነበረውን በችግር ጊዜ መጾምን ባንቃወመውና ባንነቅፈውም፥ ክርስቶስ"*ምንጊዜም ተዘጋጅታችሁ ኑሩ*" በማለት የሰጠውን ትእዛዝ እናስቀድማለን:: ችግርና ጭንቅ ሲመጣማ: የማያምነው ሁሉ ወደ ላይ እያንጋጠጠ አቤት አቤት ይላል:: ይህ ደግሞ ሠርገኛ ሲመጣ ወደ በርበሬ ቅንጠሳ መሄድ ይሆናል:: ከዚህም ጋር፥ ዓለም እኛ ባለንበት ገጿ ደህና ብትሆንም፥ በሌላው ጎኗ በነነዌ ያንዣበበው መቅሰፍትና ቸነፈር ሳይመታት ውላ የምታድርበት ቀን የለምና ጾማችሁን ጸሎታችሁንና ስለታችሁን በግልና ባካባቢ አትወስኑት ይላሉ የቀደሙ አባቶች:: ባለንበት ክፉ ዘመን በኦርቶዶክስ ሃይማኖትና በኢትዮጵያ ላይ ከውስጥና ከውጭ የሚረባረቡት ችግሮች በዚህ ስለማያልቁ ወደመልሱ እንሂድ:: የፈጣሪን መሐሪነትና የሰውን አዛኝነት የሚያሳየውን የነነዌ ጾም ከነገረ መለኮት ከታሪክና ከባህል አንጻር እንመልከት::

## ፩ኛ የነነዌ ጾም በነገረ መለኮቱ አንጻር:-

የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ተቀንጥባ በተወሰደች ዘለላ ጥቅስ ላይ የተመሠረተ ብሒል የላትም:: በኦሪትና በነብያት ሙሉ ሐሳብ ላይ የተመሠረተ ነው:: ከኦሪትና ከነብያት እልፍ ብንል "*አኀቲ ቅድስት ጉባዔ*" የምትባለው የአኀት አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ታዛቢ አለን:: የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ትምህርት ከነዚህ ሶስት መስፈርቶች አልፎ አይሄድም:: ከሄደ "እመቤታችን *በ* Immaculate conception ተጸንሳ ተወለደች" የሚለውን የጣሊያኖችን እምነትና ትምህርት

"ጥንተ አብሶ" በሚል ሽፋን እንደ አባ ማትያስ ያሉ ሰወች ከተውታል ማለት ነው:: እንደተባለውም የነነዌ ጾም የተፈጸመው ከክርስቶስ ልደት ፰፻ አመታት በፊት ነበር:: ይሁን እንጅ የዮናስን ባሳው ሆድ ውስጥ ቆይታ: ክርስቶስ በመቃብር ለቆየበት ጊዜ አንጻራዊ አድርጎታል:: (ማቴ ፲፪:፵):: ዮናስ ከአሳው ሆድ ከወጣ በኋላ ወደነነዌ ሄዶ በሦስት ቀን ውስጥ ነነዌ ትገለበጣለች እያለ ሰበከ::(፫:፬) ክርስቶስም ሰውን ለማዳን በመቃብር ውስጥ የሚቆይበትን ጊዜ ዮናስ በአሳው ሆድ የቆየውን የጊዜ መጥኖና አነጻጽሮ ስላቀረበው የነነዌ ጾም ትንሣዔውን ለምናስታውስበት ኩዳዴ (ዓቢይ ጾም) መቀበያ ሆናለች:: ለክርስትና እምነትና ትምህርት ዋና መሠረት የምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን ተስፋ ነው:: የነነዌ ጾም ተስፋ ለምናደርገው ለምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን መግቢያና ምሳሌ ሆናለች:: የጥንት አባቶቻችንም የበአላትና የአጽዋማት ማውጫ መንደርደሪያ አድርገዋታል:: የጥፋት እሳት ካንዣበበባት ዓለም የምንገላግልበትን ዳግም ምጻቱን ተስፋ እያደረግን፥ ክርስቶስ ዳግም እስኪመለስ ድረስ ምሕረቱን እያሰብን፥ ለኛ ሊደረግ የምንፈልገውን ሁሉ ለሌላው ማድረግ ባንችልም፥ ሌላውን ከመጉዳት በመጠንቀቅ፥ ሲጎዳም ለምናየው ሁሉ እንደ ዮናስ "*እኔን እኔን*" እያልን በተስፋ እንጠብቀዋለን:: የሚአስተቸውና የሚአሳፍረው ይህን ቅዱስ ሥርአት መርሳቱና አቅጣጫውን ማሳቱ እንጅ፥ መጠበቁ የሚያኮራ የእምነት የታሪክና የባሕል ባለቤትነትን የሚአሳይ ነው:: ይህን እየነገርነው የሚነቅፈንና የሚተቸን ካለ ተልእኮው ሌላ መሆኑን ተገንዝበን፥ መጽሐፍ ቅዱሱን እንደ ጋዜጣ አነበነበከው እንጅ እየደገምክ በማንበብ አልተረዳህውም፥ መሠረትህንም ለቀህልና ተመለስ! ብለን አባቶች ወደነገሩን ታሪክ እንሻገር::

## ፪ኛ የነነዌ ጾም በታሪካችን አንጻር:-

የታሪካችን ምንጭና መነሻ የሆነውን የማክዳን ታሪክ ክርስቶስ ከጾመ ነነዌ ትዝታ ጋራ በወንጌሉ እንዲህ ሲል አስተሳስሮታል:: "*በፍርድ ቀን ማክዳና የነነዌ ሰወች በዚህ ትውልድ ላይ ይፈርዱበታል*"*(ማቴ ፲፪:፵፩-፵፫)*:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የነነዌ ሰዎችን ከኛዋ ማክዳ ጋር በንጽጽር ማቅረቡ፥ በጾመ ነነዌ ወቅት እድናስታውሳት አድርጎናል:: በምናደርገው ጥሞና (meditation) ከምናስታውሳቸውም ብዙ የታሪካችን ምንጮች አንዷና ተቀዳሚዋ ይህችው ንግሥት ማክዳ ናት::

ከነነዌ ጾም ጀምሮ ያለውን ታሪካችንን እንኳን በጥሞና ብናስተውለው: ከላይ እንደተገለጸው ከነነዌ እስከ ክርስቶስ ስምንት መቶ አመታት፥ ከክርስቶስ ልደት እስካሁን ፪ሺህ ፩ አመታት፥ ድምሩ ወደ ፫ሺህ ይጠጋል:: የዛሬ መሪዎች የምናስበው ታሪክ የሌለን ታሪከ ቢሶች አርገውን ኢትዮጵያ የምትባል አገር አልነበረችም ይሉናል:: ብትኖርም አጼ ምኒልክ የዛሬ መቶ አመት የፈጠሯት ናት እያሉ ከዚያ በፊት የነበረንን ሁሉ ከአዕምሮአችን አጥበው የጋማ ከብት ሊአደርጉን የሚሞክሩ ይሉኝታ የሌላቸው ደፋሮች ናቸው:: ይህም የሚአሳየው ንስሐ በማይገባ በማይጸጸትና ሐቅን በሚያፈርስ ትውልድ ላይ ይፈርዳሉ እያለ ክርስቶስ የተናገረውን መለኮታዊ ቃል በመፈጸም ላይ መሆኑን ነው:: በነዚህ ከሐዲወች ላይ ማክዳን ዘመን ማይሽራት የታሪክ ሐውልት ሕያው ምስክር አርጎ አቁሚታል:: እነሱ እየፈጠሩ በኬሻ (ጆንያ) ውስጥ የሚከቱትን የሐሰት ታሪክ የሚሸከም ካለ፥ እንደ ጋማ ከብት ማመሳኳት የማይችል ሰው ብቻ ነው::

ከቅዱሳትና ርኩሳት እንስሳት ጋራ የምንመሳሰልባቸውና የምንለያይባቸው ብዙ ነገሮች አሉን:: ከነሱ አንዱ ከማያመሳኩት ከጋማ ከብቶች የምንለይበትና፥ ከሚአመሳኳት (ማመንዠክ) ከቅዱሳት እንስሳት ጋራ የምንመሳሰልበት ነው:: ከቅዱሳት እንስሳት ጋራ በማመሳኳት ብንመሳሰልም: እነሱ የሚአመሳኩት በማድቀቂያ (digestive) ዘይቤአቸው (ሲስተማቸው) ነው:: እኛ የምናመሳኳው በማሰቢያ አንጎላችን ነው:: በነገራችን ላይ ማመሳኳት ማለት ማመንዠክ ወይም ማንቀራጨት ነው:: አባቶች ማሰብ የሚለውን ቃል ጠበቅ ለማድረክ ሲፈልጉ ከላይ የደረደርኳቸውን ቃላት ይጠቀማሉ:: ቅዱሳት እንስሳት የሚአንቀራጩት ወይም የሚአመሳኩት ገርድፈው የዋጡትን እንደገና ወደ አፋቸው አምጥተው ሰልቀው ለመዋጥ ነው:: እኛ የምናማሳኳው (የምናስበው) የተማርነውን እምነት፥ የተነገረንንና የወረስነውን ታሪክና ባሕል ነው:: ከልጅነታችን ጀምሮ በዓለም፥ በአገራችን፥ በሕዝባችንና በግል ሕይወታችን የፈጸምናቸውንና የተፈጸሙብንን ታሪኮች ከተሸከመው አንጎላችን እየቀሰቀስን በማመንዠክ (ማመሳኳት) በማሰብ የሚጠቅመንን እያጣራን እንይዛለን:: እየደገምን በማድረግ እራሳችንን እንዳንጎዳ እርስ በርሳችንም እንዳንጎዳዳ የማይጠቅመንን እናልፈዋለን:: ትምህርት ሃይማኖት ታሪክና ባሕል የሚጠቅሙት ለዚህ ነው:: ከአጿሞቻችን አንዷ የጾመ ነነዌ ዋና መሠረታዊ ምክንያት አገራችን ያጠራቀመችውን ታሪክና ባህል፥ ቤተ ክርስቲያናችንም አበጥራና አጥርታ የያዘችውን

የተዋሕዶውን እምነት በመመርመር፥ እኛ ዛሬ የምናደርገውን ልማትና ጉዳት፥ ባለፈው ትውልድ ከተደረጉት ጋራ በጥሞና እያነጻጸርን ራሳችንን በመታዘብ በተዋሕዶ (ባንድነት) ወደ መሐሪው አምላክ ለመቅረብ ነው::

ክርስቶስ *"ይህ ትውልድ"* ብሎ ያመለከተው፥ ይህን ታሪክ ወደሚንዱት ወደዘመኑ መሪወች፥ በተለይም ወደኛ መንፈሳውያን መሪዎች ነን ባዮች ይመስላል:: ሕዝቡ ሲገደል: እምነቱ ሲቃወስ: ያገሪቱ ዳርድንበር ሲፋለስ: የተወለደባትን አገር እስከመጥላት ሲደርስ ምንም ባለመተንፈሳችን፥ ስንጠየቅም አላየንም አልሰማንም እያልን ሐሰት በመናገራችን፥ *"ማእበሉ ጸጥ እንዲልላችሁ እኔን ከመርከቡ አውታችሁ ወደ በሐሩ ጣሉኝ"* ካለው ከዮናስ ሕሊና ጋር ሕሊናችን ተጋጭቷል:: ሕዝቡን ለዚህ ሁሉ መከራና ሥቃይ የጣሉትን ቡድኖች ንስሐ እንዲገቡ አለመገሰጻችንም፥ ኢትዮጵያውያን የተገደሉበትን የጠበንጃ ምላጭ ባንስብም፥ ስበው እንዲገድሉ ትእዛዝ ከሚሰጡት ሰወች ጋር የጠበቀ ኅብረት የለንም ለማለት አፍም ቃልም የለንም:: ከዚህ ከኛ ትውልድ የከፋ ትውልድ ከዚህ ቀደም እንዳልነበረ ከእንግዲህም የሚፈጠር አይመስልም:: ከ፪ሽ አመታት በፊት *"በፍርድ ቀን ማክዳ በዚህ ትውልድ ላይ ትፈርደበታለች"* ሲል ክርስቶስ ጣቱን የጠቆመበት ትውልድ፥ እኛ ላንሆን እንችላለን ብሎ የሚጠራጠር ካለ የታሪክ: የሞራል፥ የባሕልና የብሔራዊነት ዲቃላ ነው::

ከማክዳ ጀምሮ እኛ አፍራሾች እስከተፈጠርንባት እስከ ዚች ዘመን ድረስ የነበሩ ሰወች በደማቸውና ባጥንታቸው እየካቡ ያለፉትን ታሪክ በመናዳችን የሚመጣብን ፍርድ፥ ነፍስንና ሥጋን አንድ አርጎ የሚበላ: ከገሐነም እሳት የበለጠ እሳት ነው:: በሞራል በሽታ የደነበዘ ካልሆነ በሕሊናችን ውስጥ ይህ እሳት መንደድ መጀመሩን የገዛ ሕሊናችን ሊነግረን ይገባዋል:: በሚከተለን ትውልድ ፊትም እራቁታችንን ቆመን ከሚሰነዝርብን ፍርድ የምናመልጠበት መውጫ ቀዳዳ አይኖረንም:: ከዚህ ወረርሽኝ በሽታ እንድንፈወስ ጠበል የሚረጨን እንደ አቡነ ጴጥሮስ ያሉ የመንፈስ የሞራልና የታሪክ ሰወች አገራችን ኢትዮጵያ ጸንሳ እስክትወልድ ድረስ የመከራው ዘመን የሚአጥር አይመስልም:: በተለይ በቤተ ክርስቲያናችን ባንድምታው ጉባዔ ትምህርት ተሳትፈናል የምንል ሰዎች: የነነዌ ሰወችና ማክዳ በሚፈራረዱበት በታሪክ ሚዛን እራሳችንን መዝነን ከታሪክ ፍርድ ለማምለጥ አሁንም እድሉ ከፊታችን ነው::

ክርስቶስ መጥቶ ምድራዊ ታሪካችን በሰማያዊው ታሪክ እስኪተካ ድረስ: ስለዘላቂው መንፈሳዊው ሕይወታችን፥ ከኛ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ ስለምናስረክበው ታሪካችን፥ ስለጠቅላላዋ ኢትዮጵያችን ዳር ድንበር ጥሞና ከምናደርግባቸው ወቅቶች የነነዌ ጾም አንዷ ናት:: እግዚአብሔር አልባ ከሆኑት ሰዎች ግንዛቤ በቀር: ፍጥረት ያለፈጣሪ እራሱን አላስገኘም:: እኛ ኢትዮጵያውያን በየዘመኑ የተጻፉው ታሪካችን በፈጣሪ ቸርነትና ረድኤት እንደተፈጸመ እናመናለን:: ስሜታችንና ታሪካችን በዚሁ የተቀረጸ ነውና፥ ይህን ሁሉ እያሰብን ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ የነይነይን (ነነይ) ጾም እየጾምን እንጠብቀዋለን::

## ፫ኛ የነነዌ ጾም በባሕላችን አንጻር:-

*"ቀኝና ግራቸውን ለይተው ያላወቁ ሕጻናትና ብዙ እንስሳት ለሚኖሩባት ከተማ ለነነዌ አላዝንምን? (፬:፲፩)* ብሎ እግዚአብሔር የተናገረውን፥ ነቢዩ ዮናስም *"ማእበሉ ጸጥ እንዲልላችሁ እኔን አውጥታችሁ ወደ ባሕሩ ጣሉኝ" (፩:፲፪)* ሲል የተናገረውን፥ እንደገና ደግሞ የመርከቡ ሰዎች *"የዚህ ንጹሕ ሰው ደምም በእኛ ላይ አይሁን"(፩:፲፬ )* ሲሉ የተናገሩትን ሁሉ አባቶች ከስሜታችንና ከባሕላችን ጋራ አዋሕደው በመቅረጽ ለእኛ ሰርተውልን ነበር:: እኛም ከራሳችን መንፈሳዊ ታሪካዊና ባሕላዊ አካል ጋራ አዋሕደናታል:: ዮናስ "እኔን አውጥታችሁ ጣሉኝ፥ እናንተን ለማዳን እኔ ልጎዳ እኔ ልሙት" ያለው በልባችን ስለተቀረጸ እንኳን ሰው እንስሳ እንቅፋት መቶት ሲወድቅ ባካባቢያችን ብናይ *"እኔ ልውደቅልህ: እኔ ደፋ ልበልልህ፥* እንል ነበር:: ህም የሚአሳየው የኛ ባሕል በነብያት ስሜትና በፈጣሪ ቸርነት የተቀረጸ መሆኑን ነው:: ይህም መለኮታዊና ሰባዊ ርኅራኄ "divine and human compassionate system" ሲባል ኖሮ ነበር:: በተቃራኒው አብዛኛው የምዕራቡ ባሕል ያሸነፈ ይኑር (*survival of the fittest*) በሚለው ዘይቤ ላይ የተመሰረተ ነው:: በመሆኑም በምዕራቡ ዓለም ዘንድ "ልውረርህ አንተ ሙትልኝ የሚል እንጅ *"እኔ ልሙትልህ"* የሚለው የኛ ስሜት እጅግ የታወቀና የተለመደ አይደለም:: ሌላው ቀርቶ ራሳቸው ምዕራባውያን ምሑራን ይህንኑ ባሕላቸውን በስስት ላይ የተመሰረተ የኑሮ ዘዴ (greedy comercial system) ብለውታል:: በዚህ ዘመን ያለን ኢትዮጵያውያን ባለመታደላችን ከዚህ መንፈሳዊና ሰባዊ ስሜታችን ጋር የሚጻረረው የምዕራቡ ያኗኗር ስልት በጥቂት ስስታም ኢትዮጵያውን አማካኝነት

ወደኛ አገር ተሻግሮ ሕዝባችንን እያሰቃየው ነው::

አንድ ነገር መጀመሪያ ከነበረበት ቦታ ተነስቶ በደረሰበት አገር ሕዝብ ተደጋግሞ ለብዙ ዘመናት ሲደረግ ከኖረ፥ ተቀብሎ ለሚያደርገው ሕዝብ ባሕል ይሆናል:: ካካባቢው ጋራ መዛመድን ሲያተርፍ፥ በነበረበት ቦታ የነበረውን ስም አጠራር እንደነበረ አይጠብቅም:: በመሆኑም በጥንቷ ባቢሎናዊት ከተማ ስም በያመቱ የምንጾማት የነነዌ ጾም ስሟን ቀይረን ግማሾቻችን "ነይ ነይ" እንላታን:: ሌሎቻችንም "ነነይ" እያልን የባሕላችን አካል አድርገን ይዘናታል:: እንዲህ አይነቱ በፈጣሪ መሐሪነትና ሰብአዊ ስሜት ላይ የተመሰረተው ባሕላችን በየእለቱ ኑሮአችን ላይ ቢታይም፥ በተለይ በጾመ ነነዌ ሰሞን እጅግ በጣም ጎልቶ የሚነገርና ጥሞና የሚደረግበት ነበር:: ስለነነዌ ጾም የሚጠይቁ ሰዎች በውጭ ተወልደው ያደጉ ወይም የውጭ ዜጎች ካልሆኑ ወይም ባንዳንድ ምክንያት የማሰብ ችሎታቸውን ካላጡ በቀር ከነነዌ ጾም ጋራ የተሳሰረው ኢትዮጵያዊ ስሜት ከሕሊናቸው ጨርሶ የሚጠፋ አልነበረም:: ከጠፋባቸውም እንጀራውን መብላት እንጅ ጤፍ ተዘርቶ ሲበቅል ሲታጨድ፥ ሲወቃ፥ ሲፈጭ እያዩ ያላደጉ"*ጤፍ የሚለቀመው ከዛፍነው ወይስ ከበሐር?*" ብለው ጠየቁ እየተባለ ከሚነገርላቸው ኢትዮጵያውያን ልጆች የማይለዩ መሆናቸውን የሚአስገነዝብ ነው::: ማመሳኳት የምንችል በዚህ ዘመን ያለን ኢትዮጵያውያን ተባብረን፥ ይህ በብዙ አቅጣጫ ሰርጎ የገባው የመዘንጋት፥ የጥፋትና የጭካኔ ስሜት፥ የኛ አለመሆኑንና እንዲታረም ሳንጮህ ዝም ብለን ካለፍነው፥ የነበረውን ቅዱስ ባሕል ተክቶ ለሚቀጥለው ትውልድ ባሕል ሆኖ የሚቀር መሆኑ የሚአጠራጥር አይደለም::

ይህን ሁሉ ለሚታዘብ ዜጋ ነነዌ ላይ ያንዣበበውን መከራ በኢትዮጵያ ላይ ከወረደው መከራ ጋራ እንዴት ማነጻጸር ይቻለዋል? የኢትዮጵያ ሁኔታ ከነነዌ እጅግ መባሱ፥ የአዲስ አበባም ሁኔታ ዮናስ ከተሳፈረባት መርከብ እጅግ በጣም መክፋቱ እንኳን ኢትዮጳውያንን በሩቁ ሆኖ በመመልከት ላይ ያለውን ዓለም እያስገረመው ነው:: በነነዌ ላይ መከራ አንዣበባት እንጅ አልወረደም ነበር:: እንኳን የሰው ሕይወት አንዲት የዛፍ ቅጠልም አልነተነካች ነበር:: መርከቧ በማእበሉ ተናውጣ ሽቀጡ በባሕሩ ቢሰምጥም የአንድ ሰው አካል አልተጎዳም ነበር:: በኢትዮጵያ ላይ እየወረደ ያለው መከራ ግን ለታሪክ ለድንበር ለእምነትና ለባህል ምስክነት ጎልተው የሚታዩትን አዛውንቶቿን እየፈለገ የሚበላ፥ ጥርሳቸውን ፈልጎ ዝሆኖችን አድኖ የሚገድል፥ ቆዳቸውን ተመኝቶ ነብሮችን የሚአጠፋ የጥፋት ማእበል ነው:: እርግጥ ነው:: ዛሬ አገሪቱን በመግዛት ላይ ያሉት ኢትዮጵያውያንን በመግደል ፍጹም ርካታና ደስታ የሚሰማቸው ቀኝና ግራቸውን ለይተው ያላወቁ ሕጻናትን በመቅሰፍ የማይጸጽታቸው፥ ለአገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን መሠረት መሆን የሚችሉትን ወጣቶች የሚውጡ፥ ቅዱስ ጊዮርጊስ የገደለው የቤሩቱ ደራጎን ባሕርይ የተጠናወታቸው ጎሾወች ናቸው::

አሁን እንኳን ሳይቀር ከሞት የተረፉትን ኢትዮጵያውን ወጣቶች ከትምሕርት ገበታቸው እያወጡ ከእንስሳት ጋራ እንዲውሉ እያደረጓቸው ነው:: ከሕሊናቸው ጋር ያሉትን ኢትዮጵያውያን ምሑራን ከዩኒበርስቲዎችና ከኮሌጆች እንዲወጡ እያስገደዷቸው ነው:: የሚሰበከው የዘር ፖለቲካ ኢትዮጵያውያንን እያናወጠ፥ ድንበር እያፈረሰ ሕዝቡን እያተራመሰው ነው:: ታዲያ የመጣባት መከራ ለሶስት ቀን ብቻ ያንዣበባትን ነነዌን ፲፰ አመታት ሙሉ በጎሾዎቿ ጥይት እተናወጠችና እየተቆላች ካለችው ኢትዮጵያ ጋር እንዴት እናነጻጽራታለን?

ዮናስ ከተሳፈረበት መርከብ ወደ በሐሩ እንደተጣለው ሽቀጥ፥ መአስባን (ሕጋውያን) ማለትም በተቀደስ ጋብቻ የተወሰኑ ሊቃውንት ካሕናት ከቤተ ክሕነቱ ወደ ውጭ እየተጣሉ ናቸው:: በነዚህ ሊቃውንት ይተዳደሩ የነበሩት መምሪያወችና አድባራት፥ ሳይማሩ ሳይመንኑ የነ እንጦንስንና መቃርስን ቆብ አስመስለው ሰፍተው ባጠለቁ ወንደ ላጤወች እየተሞሉ ናቸው:: ወጣቱ የተቀደሰውን ጋብቻ እንዲጠላ ወንደ ላጤነትን እንዲቀበል እየተሰበከለት ነው:: ከችግር ለማምለጥ ቆቡን እያደረጉ ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡት ብዙወቹ "*ይህችን ዓለም ናቃት ሸሻት መንናት፥ ከጮማዋ ከጠጇ ራቅ! አሸዋ ቅመህ ቅጠል ቆርጥመህ ኑር!*" ከሚለው ምንኩስና ባሕርይ ጨርሰው በመራቅ ጥቂሩን ልብስና የምንኩስናውን ቆብ እንደሽፋን ተጠቅመው ቤተ ክርስቲያንን በመዝረፍ የራሳቸውን ሕንጻ እየገነቡ ናቸው:: ዘርፈው የሚወስዱት ገንዘብ ሲአንሳቸው ምእመናኑን በመክሰስ በየአደባባዩ እየጎተቱት ነው:: የኢትዮጵያውያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውት አባቶች "*ጥንተ አብሶ*" በማለት እያስተማሩ ያለፉት በሕዝብ፥ በአገርና በቤተ ክርስቲያን ላይ ጠላት የሚፈጽመውን ይህን መሳይ ግፍና ሥቃይ ነበር:: አሁን በአቡነ ጳውሎስ ዘመን እመቤታችን በ"*Immaculate conception*" ተጸንሳ ተወለደች የሚለውን የካቶሊኮችን ትምህርት "*ጥንተ አብሶ*" በሚለው የተተካውን አልነበረም:: እንዲህ የመሰለውን

የተዋሕዶውን ነገረ መለኮት የሚአፈርስ ኢኦርቶዶክሳዊ የሆነ ትምህርት ባብነቱ ጉባያቸው ኢትዮጵያውያን አበው ፈጽመው አላስተማሩንም:: ይልቁንም በመላ ኦርቶዶክሳውያንና በኛ አባቶችም ሊቃውንት የተጠላና የተወገዘ ነው::

በአገራችንና በቤተ ክርስቲያናችን ላይ እየተፈጸሙ ካሉት ከነዚህ ሁሉ ውዥንብር መከራና ሥቃይ አንዷ እንኳን በነነዌ ላይ አልደረሰም:: ቤተ ክርስቲያናችንስ ቢሆን ከደረሰባት መከራ አንጻር ከነነዌ ጋር እንዴት ትነጻጸራለች? በነነዌ ላይ ሊደርስ የነበረውን እልቂት ዮናስ "*እኔ ልቅደም እኔ ልውደቅ፥ እኔ ልሙት*" ብሎ ሕዝቡን ለማጥፋት በመጣው ማእበል ውስጥ እራሱን መጋረጃ አድርጎ በመክተቱ: በሕዝብ ላይ ከመፈጸሙ ማእበሉን አግዶታል:: በቤተ ክርስቲያናችን መርከብ ላይ ተሸራሽተው የተሳፈሩት አባ ጳውሎስ የዮናስን መንፈሳዊና ሰባዊ ስሜት በጥሞና ተረድተው ቅዱስ አባታችን ለሚላቸው ሕዝብ በናንተ ላይ የሚጎርፈው የመከራና የስቃይ ማእበል ጸጥ እንዲልላችሁ "እኔ ልቅደም እኔ ልሙት" በማለት ላይ ናቸው? ወይስ በፍቅረ ነዋይና በፍቅረ ሢመት የኑሮ ዘዴ ተውጠው፥ ራሳቸው የሚፈጽሙት ደባ ሳያንስ፥ "ከኛ በፊት እናንተ ደፋ በሉ" በሚለው በዚሁ ስሜታቸው ጳጳሳትን ቀሳውስትንና መነኮሳትን እያሰለጠኑ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን በመሰግሰግ ላይ ናቸው?

"*የበሐሩ ማእበል ጸጥ እንዲልላችሁ እኔን ወደ በሐሩ ጣሉኝ*" ሲል ለሰው ልጅ ባሳየው ርህራሄ፥ ዘጠኝ ወር ከተኛበት ከናቱ ማሕጸን የተመቼ ያሳነበረ ሆድ ለዮናስ ያዘጋጀውን እግዚአብሔርን ለረሳችሁ ሁሉ ወዮላችሁ! ባገራችንም ሆነ በቤተ ክርስቲያናችን ኢሰባዊ በሆነ አመራር ውስጥ ተሸጉጣችሁ ከጥርሳም አሳ (ሻርክ) በከፋ *መንጋጋችሁ* ያለውን ይህን ትውልድ ብቻ ሳይሆን *መጭውንም* ትውልድ በመብላት ላይ ያላችሁ ሁሉ! የምትፈጽሙትን መከራና ግፍ አሁን ካላቆማችሁ ከዚህ በፊት ላደረጋችሁት በደልም ንስሐ ካልገባችሁ! ከናንተ *መንጋጋ* እጅግ የሰላና የከፋ ሌላ *መንጋጋ* እንደ ሚጠብቃችሁ የፈጣሪና የተፈጥሮ ሕግ እንደሆነ በኢትዮጵያዊ ስሜቴና በተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅስናየ አሳስባችኋለሁ:: ይቆየን

ለብርሃነ ትንሳኤው ያድርሰን!

ቀደም በዚህ ጽሁፉ ደራሲ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ወቅቶች የተጻፉትን ጦማሮች ለማንበብ የፈለጋችሁ ሊንኩን መመልከት ትችላላችሁ::

http://www.ecadforum.com/files/Timiqet.pdf

http://66.92.66.199/abugidainfo2009/wp-content/uploads/2007/08/shimiglina1.pdf

http://www.divshare.com/download/6799363-258

http://www.divshare.com/download/6799363-258